# ጋለሪኣ ቶሞካ

## መክሊት መርሻን ያቀርባል

GALLERIA TO.MO.CA. PRESENTS Meklit Mersha



የፎቶግራፍ ትርዒት

# አድናቆተ ተፈጥሮ

ሰኔ 21 2005 ዓ.ም.

A Photography Exhibition

# Nature's Sensation

June 28/2013

# ጤና ይስጥልን!

**እንኳን ወደ ቶሞካ ቤተሥዕል ማሳያ ሁለተኛው የፎቶግራፍ ትርዒት በደህና መጣችሁ!**

**የፎቶግራፍ ጥበብ ባለሞያዎችን ከጥበብ አድናቂዎች ጋር የምናገናኝበት መድረክ ባለፈው ወር በፎቶግራፈር አይዳ ሙሉነህ ሥራዎች ተጀምሯል፡፡ ብዛት ያላቸው የጥበቡ አፍቃሪዎችም ፎቶግራፎቹን ሲጎበኙ ገንቢ አስተያየቶቻቸውንም ሲሰጡን ቆይተዋል፡፡ እነሆ በዚህ ወር ደግሞ ሌላ የጥበብ ድግስ ከጋለሪኣ ቶሞካ ቀርቦላችኋል፡፡ ወጣት የፎቶግራፍ ባለተሰጥዖዋ መክሊት መርሻ ሥራዎችዋን ለጥበቡ አድናቂዎች ታቀርባለች፡፡ የፎቶግራፍ ጥበብ ለማኅበራዊ ለውጥ ቢውል ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል የምትለውና የ"ቪዥዋል ሶስዮሎጂ" (የዕይታዊ ነገረ-ማኅበረሰብ) ባለሙያ የመሆን ግብ ያላት መክሊት ብዛትያላቸው ማኅበራዊ ጉዳዮችን የዳሰሰችባቸው ፎቶግራፎች ከቶሞካ ትኩስ ቡና ጋር እነሆ ትለናለች፡፡**

**በትኩሱ የቶሞካ ቡና በልባዊ የፎቶግራፍ ጠበብት ሥራዎች ክረምቱን ዘና ይበሉ!**

**የፊት ሽፋን**

**የአትክልት ቦታዬ,** 2003 **ዓ.ም.**

(On the cover)
My Garden
Addis Ababa, Ethiopia
2013

June 30/2013
Presented by Galleria TO.MO.CA.
Art Director - Eshetu Tiruneh
Communications - Mifta Zeleke
Editor - Nebiyu Girma
Printed by Central Printing Press

# WELCOME NOTE

Welcome back to another exciting month of art feast at Galleria TO.MO.CA. The first photography exhibition featured the works of Aida Muluneh. Art lovers have been visiting the pictures and expressing their appreciations. We've also received constructive feedback from art lovers visiting the gallery. Young and aspiring Photographer Meklit Mersha is showing exquisite talent in the month of June. Meklit is an advocate of photography for social change. She also aspires to be a visual sociologist.

Take pleasure of the rainy season with hot TO.MO.CA. Coffee and with passionate photographers' pieces!

**ይዘት**

**የሕያውና የግዑዝ ብሌናች መስተጋብር ፭**

**ነገረ ማኅበረሰብ ፎቶግራፈር ⁝መክሊት ፲**

Contents

Concurrence Of The Animate
& The Ideal Lenses 5
Meklit: "The Visual Sociologist" 11

# የሕያውና የግዑዝ ብሌኖች መስተጋብር፤ /ቁጥር ሁለት/

መክሊት መርሻ በቶሞካ ቤተሥዕል ማሳያ የክረምት ወቅት ከሚቀርቡት የፎቶግራፍ ትርዒት ዝግጅት ሁለተኛዋ ተሳታፊ ናት። የፎቶግራፍ ትርዒቷ በጥቅሉ ሲታሰብ ዐውደ ሐሳብዋ የሚያጠነጥነው በሁለንተናዊው የተፈጥሮ ገጽታ ዙሪያ ነው። በተናጠል ካየነው ደግሞ የተፈጥሮ ንዑስ ክፍልን፣ በጣም የንዑስ ንዑስ ክፍልን ገጽታ ነው። ይኸውም የዕፅዋትን በተለይም የአበባዎችንና የበራሪ ነፍሳትን ገጽታዎች ነው። ቀደም ሲል ከታየውም የአይዳ ሙሉነህ የፎቶግራፍ ትርዒት የምትለየው በዚሁ ነው።

በማለዳው የወጣትነት ዕድሜ ላይ የምትገኘው መክሊት መርሻ በልጅነትዋ ሥዕል የመሣል ፍላጎቷና ጉጉቷ ከፍተኛ እንደነበር ዛሬም ታስታውሳለች። በዚያ የልጅነት ጊዜዋ ነበር የፎቶግራፍ ማንሳት ዝንባሌ የታየባት። /ግለታሪኳ ንደሚመለከቷል።/ ምናልባትም ያኔ በሥዕል የተለኮሰው የጥበብ እሳትና የጥልቅ ውስጣዊ ስሜትና ፍቅር በጊዜው ብርሃኑ መገለጫና መውጫ ቢያጣ ለዓመታት ነበልባሉ ሳይጠፋና ፍሙ ሳይተረኮስ ከርሞ ዛሬ በፎቶግራፍ በኩል ጥበባዊ ወገግታው በራና ታየ ለማለት እንችላለን። ምንም እንኳን በዚህ የፎቶግራፍ ትርዒት ላይ የቀረቡት ዕይታዊ ምስሎች በአብዛኛው ከተክሎች ሕይወት ጋር የተጣመሩ ቢሆንም ያላት ሙያ ግን ሌላ ነው። መክሊት መርሻ በአሁኑ ጊዜ በነገረ ማኅበረሰብ /Sociology/ ትምህርት የመጀመሪያ ድግሪዋን የያዘች ባለሙያ ነች። የፎቶግራፍ ማንሳት ፍቅርዋ ግን ዛሬም ድረስ ያለና ጎን ለጎን የምታቀሳጥፈው ተግባር በመሆኑ ከተመረቀችበት ሙያ ጋር ተጣምሮ ለሌላ አዲስ ዓላማና ግብ አዘጋጅቷታል ተዘጋጅታለችም።

# Concurrence Of The Animate and The Ideal Lenses / No. Two/

Meklit Mersha is the second Photographer to showcase her photography works at Galleria TO.MO.CA this season. The general theme of her photographic exhibition is nature. If you specifically delve into her works, she shows us her fascination with plants and insects image. This is the peculiar feature of her works that differentiates her exhibition from last month's feature by Aida Muluneh.

Meklit's passion for drawing as a child was very strong as stated it in her bio. That was when she found out about her inclination for photography. That raw talent and passion may have been hidden fermenting inside her until she got the chance to finally put it in practice and just got it displayed to all art lovers.

Looking at her photographic works showing wide variety of plants, one may guess that she at least has some proximity to the biological sciences. But that is not the case. Meklit is actually a sociology graduate from the Addis Ababa University. And she is determined to use this knowledge of society in her photography. Meklit envisions being a



Water Drop, 2013 የውሃ ጠብታ, 2005



Water Drop, 2013 **የውሃ ጠብታ**, 2005

ይኸውም በነቢብም በገቢርም ወይም በማስተዋልም በጥበብም የዕይታዊ ነገረ ማኅበረሰብ /Visual Sociologist/ ባለሙያ ለመሆን ቆርጣ ተነስታለች:: በእርግጥም ሙያው በሀገራችን በዓይነቱ የተለየ መስተጋብር የሚከሠትበት ታላቅ ምኞትንና ግብን ያነገበ ራዕይ ነው::

እስቲ ይታያችሁ ወደፊት በመክሊት መርሻ በኩል የማኅበረሰቡ ማኅበራዊ ግንኙነትና ትስስር በቃለ ጽሑፋዊ ጥናት ብቻ ሳይሆን በፎቶግራፋዊ ምስል ታግዞ ወይም ሙሉ ለሙሉ በዕይታዊ ገጹ ብቻ ፍንትው ብሎ ማኅበራዊና ጥበባዊ ውበቱ ሲቀርብና ሲገለጽ የሚያገኘውን ደስታና እርካታ

visual sociologist in order to bring about social change. This definitely is an initiative that has not been practiced in Ethiopia. It's a vision that would bring so much to the industry and the country.

Imagine a showcase of the various social fabric, changes and trends being photographed and displayed by Meklit. This is a very different culture and thinking that leaves the traditional presentation of social observation and studies through literature. The photographs could



Debre Zeyit, Kuriftu, 2012 ደብረ ዘይት, ኩሪፍቱ, 2004


አይታያችሁም? ምን ይሄ ብቻ በዕይታዊ ገጹ ዘመን ተሻጋሪ የማኅበረሰቡ ምስልና ቅርስ እንደሚሆንም ጭምር ከወዲሁ አይታያችሁም? አዎ ረጋ ብላችሁም አስቡትም ተገንዘቡትም እላለሁ:: መክሊት መርሻ ዛሬ በሐሳብም በአካልም ገና ወጣት ነች:: ወደፊት በሕይወት የዕድሜ ጉዞዋና በኑሮ ገጠመኝዋና ልምዶቿ አጎልብታ አንድ ላይ ስታቀናብረውና ስታከናውነው ምን ዓይነት የዕይታዊ ነገረ ማኅበረሰብ ፎቶግራፎች ሀብት ለሰው ልጅና በተለይም ለምትኖርበት ማኅበረሰብ እንደምታስቀር መገመት አያዳግትም:: ሊደነቅም ሊመሰገንም የሚገባው ታላቅ ምኞትና ራዕይ ነውና ትጋቱንና ብርታቱን እንድታገኚ መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ::

መክሊት መርሻ ያቀረበቻቸው የዕፅዋት በተለይም የአበባዎችና የበራሪ ነፍሳት የፎቶግራፍ ምስሎችና

even be passed on to generations carrying social meanings and history. This is a vision and ambition that should be commended and applauded for. May God help you succeed in this wonderful path of creativity and mastery of nature!

Meklit's nature photographs especially the flowers and the butterflies speak volumes when you look at them from the visual art perspective. If you closely look at;

- The shots of the flower's bud, the pollen, the lines of the leaves and the decorative elements,



Hawassa, 2013 ሐዋሳ, 2005

ገፅታዎች ከዕይታዊ ጥበባት ግንዛቤ አኳያ የሚያመላክቱን ውበት አላቸውና ትኩረታችንን አንንፈጋቸው። ይኸውም

- በቅድሚያ ጥልቀትና ርቀት ሳይኖረው ጠጋ ብላ ያስቀረቻቸው የአበባዎቹ ቀንበጦችና የዘር አንቴናዎች፣ የቅጠሎቹ ሥሮችና የበራሪ ነፍሳቶቹ ሽልማዊ ንቅሶች የውሃ ጠብታዎቹ በልዩነትና በአንድነት ተስተጋብረው የፈጠሩት የመስመራዊ የዝርጋዊና የቅርፃዊ ምስሎች ግን ሕያውና ቅጽበታዊ እንቅስቃሴዎች፣
- በሁለተኛ የዛፎቹ፣ የአበባዎቹና የቅጠሎቹ አልፎም የበራሪ ነፍሳቶቹ ውጫዊ ቅርጾች፣
- በሦስተኛ አበባዎቹና ቅጠሎቹ ያላቸው ሕብረ ቀለማዊ ኅባሬዎችና ነጸብራቆች

the water drops and the shaped images she took reflect the specific movements and memorable moments.

- The unique external features and shapes of the trees, flowers, the leaves and the insects.
- The harmonious colors and reflections of the flowers and the leaves
- The harmony of light and dark features of the surroundings
- All these features have tremendous beauty and artistic value remaining ingrained in our mind.



My Garden, 2011 የአትክልት ቦታዬ, 2003

- በአራተኛ የሕብረ ቀለማዊ የብርሃንና የጭለማ ደጀናዊ ድባቦች፣

በዓይነኅሊናችን ላይ የሚያስቀሩት ውበታዊ ጣዕም አላቸው፡፡ ይህ ትርዒት የመክሊት መርሻን የፎቶግራፍ ጥበባዊ ዕውቀትና ችሎታ ብቻ ሳይሆን የሚያስገነዝበን ብቃቷንና ጥረቷን ጭምር ነው፡፡ አሁንም በርቺ ጎብዢ እያልኩ ቶሞካ ቤተ-ሥዕል ማሳያ ደግሞ ከጣዕመ ቡና ጋር ጣዕመ ጥበብን እንድናጣጥም ስለአመቻቻችሁልን ከምስጋና ጋር ጎሽ፣ አሰይ፣ ቀጥል እላለሁ፡፡

እሸቱ ጥሩነህ /ሠዓሊ/

All these artistic observations tell us that Meklit indeed is well versed in her knowledge of photography and art. It also shows her ability and relentless effort to connect to nature and show her understanding to all of us. I salute Meklit and want to say well done and do more of what you're doing! I also want to thank Galleria TO.MO.CA. for putting together the show along with the exotic taste of Tomoca Coffee. Good Job and Carry on with your marvelous efforts !

Eshetu Tiruneh



My Garden, 2011 የአትክልት ቦታዬ, 2003



# ነገረ ማኅበረሰብ ፎቶግራፈር፧ መክሊት

ጠንካራ ጓደኝነትና ማኅበራዊ ግንኙነት መመሥረት የመክሊት ድንቅ ችሎታዎች ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለ ማኅበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጽታዎችና ስለተፈጥሮ በፎቶግራፎች ውስጥ በመግለጽ በኩል ግን ችሎታዋ ልዩ ነው፡፡ የተለያዩ ቦታዎችን የመጎብኘት እንዲሁም ለሕይወትና ለተፈጥሮ ያላት ትልቅ ፍቅር የፎቶግራፍ ችሎታዋን ቅርጽ ለማስያዝ በእጅጉ እንደጠቀማት ትናገራለች፡፡ በፍልስፍና እና መንፈሳዊ ጉዳዮች የሚጽፉ እንደ ፓውሎ ኮኤልሆ፣ ኤካርት ቶሌ እና ቪንሰንት ኖርማንን የመሳሰሉ ደራሲያን ጽሑፎችም ለሥራዋ ሁነኛ መነሳሳትን እንደሚሰጣትና በሳል የፎቶግራፍ ውጤቶችን እንድትሠራ እንደሚረዳት ታነሳለች፡፡ የመክሊት የሥነ-ሥዕልና ፎቶግራፍ ፍቅር ታሪክ ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለች ትወስድ ከነበረው የሥዕል ክፍለጊዜ ይጀምራል፡፡

“በክፍል ውስጥ ጥሩ የሥዕል ችሎታ ካላቸው ተማሪዎች መካከል ቀዳሚዋ ነበርኩ፡፡ ወደ አእምሮዬ የሚመጡ የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን መፃፍም እወድ ነበር፡፡ የእኔ እናት አትክልት መንከባከብ በጣም ትወድ ነበር፡፡ ግቢያችን በሚያማምሩ አትክልቶች የተዋበ ስለነበር ተፈጥሮን ለማድነቅና ለመረዳት ጥሩ ዕድልን ሰጥቶኛል፡፡ የምሥላቸው ሥዕሎችም ወደዚያ ያደሉ የነበረው በዚህ ተጽዕኖ ይመስለኛል፡፡” ትላለች፡፡ “ሁለተኛ

## Meklit: “The Visual Sociologist”

Socializing and group activities may not be her best qualities, but Meklit Mersha surely knows how to show the different social fabrics and nature in her fascinating pictures. Her love for travelling, nature and excitement to life in general shaped her photography skills. The spiritual books written by authors like Paulo Coelho, Eckhart Tolle and Vincent Norman also give her the inspiration to do what she does best; showing her fascination for nature with pictures.

Mekilit’s love for drawing and photography goes way back to her elementary school drawing class. “I used to be one of the top students who had good skills to draw. I also loved writing stories” says Meklit. The garden, her mother fondly used to take care of at their compound, also got her very close to nature. She got her first cell phone when she went to high school at Nazareth School

ደረጃ እንደገባሁ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ሞባይል የያዝኩት፡፡ ሞባይሌ ካሜራ ስለነበረው ፎቶ ከማንሳት በቀር ሌላ ሥራ አልነበረኝም ጓደኞቼን፣ ትምህርት ቤት ውስጥ የማያቸውን ነገሮች ሁሉ ሳነሳ ነበር የምውለው፡፡ አንዳንድ ጓደኞቼ እንደውም የማነሳቸውን ፎቶ በጣም እየወደዱት እያሳጠቡ ሁሉ እቤታቸው ይሰቅሉት ነበር፡፡”

“ሌላው የፎቶግራፍ ፍቅሬ መሠረት የሆነው ከውጪ አገር ታትመው ይመጡ የነበሩ ባለ ሕብረ-ቀለም መጽሔቶች፤ በተለይ የፋሽኖቹ ነበሩ፡፡ መጽሔቶቹ ቤት ስለሚገዙ በጣም እከታተላቸዋለሁ፡፡ በኋላ ላይ ሳስተውል ግን ከፎቶግራፎቹም ባሻገር በፎቶዎቹ የሚያርፈው ብርሃንና ጨረር ውበት በጣም እየሳበኝ በትኩረት በማየት አሳልፋለሁ፡፡ እንደዚህ ባለ ጥራት እና ውበት የሚነሱ ፎቶግራፎችን ማንሳት በጣም እመኝ ነበር፡፡”

እንዲህ በሐሳብ ያየችውን ለመተግበር አንድ እርምጃ የሚያራምዳትን ስጦታ ከአጎቷ አገኘች - ፕሮፌሽናል የፎቶ ካሜራ፡፡ ያኔ 17 ዓመቷ ነበር፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ስትቀላቀል ደግሞ በአዲስ ዓይን የፎቶግራፍ ጥበብን ማየትና ችሎታዋንም ማሻሻል ጀመረች፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ ስትከታተል የነበረው የነገረ-ማኅበረሰብ (ሶስዮሎጂ) ትምህርት ማኅበረሰባዊ ጉዳዮችን በካሜራዋ እንድትዳስስ ዕድሉን ሰጣት፡፡ የመጀመሪያ የፎቶግራፍ ትርዒቷን ከተለያዩ የማኅበረሰብ ጥናት ጋር የተያያዙና ከጎዳና ላይ የተነሱ ፎቶግራፎችን በማሰባሰብ አቀረበች፡፡ ይህ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ በነበረችበት ወቅት ያቀረበችውና ከምትወስደው ኮርስ ጋርም የተያያዘ ነበር፡፡ የ22 ዓመቷ መክሊት በ2004 ዓ.ም. ከዩኒቪርሲቲ በነገረ-ማኅበረሰብ (ሶስዮሎጂ) ተመርቃለች፡፡ ይሁንና በቀጥታ በሞያው ከመሥራት ይልቅ ፎቶግራፍን የሙሉ ጊዜ ሥራ አድርጋ ይዛለች፡፡ ትምህርቱም ታዲያ ብክነት አልሆነም፡፡ ሁለቱን አቀናጅታ የዕይታዊ ነገረ-ማኅበረሰብ ባለሙያ (ቪዥዋል ሶስዮሎጂስት) የመሆን ሰፊ ዕቅድን ይዛበታለች፡፡ የፎቶግራፍ ጥበብንም ለማኅበራዊ ለውጥ ለመጠቀም ታስባለች፡፡

ነብዩ ግርማ

in Addis Ababa. “The cell phone had a camera with it. That really defined my journey to photography. I was so in love with the cell phone that all I did all day was taking pictures at school, home and everywhere.” Her friends use to love the pictures she takes of them. “Some of them even printed those pictures and hang them on the walls in their room. It was a wonderful experience.”

The fashion magazines lying around in the house were also sources of inspiration for Meklit as she got older. “I wanted to be able to create images that looked amazing as the ones in the international magazines. After a while, I realized that it was not only the photographs that caught my attention, but anything that glowed with the beauty of light reflected upon it” recalls Meklit.When she turned 17, Meklit got her first professional Camera as a gift from her uncle. That was when she took the next step of taking professional pictures. Mekilit's skills got even sharper after she joined Addis Ababa University to study sociology. Her studies gave her angles to focus on. Meklit presented her very first exhibition on street photography that related to the different sociological theories and approaches. That was actually the course theme she was taking as a second year student. 22 year old Meklit graduated from Addis Ababa University last year as a sociologist. But she took photography as a full time job. She is aspiring to become visual sociologist using photography as a tool for social change.

Nebiyu Girma



ጋለሪኣ ቶሞካ
አድራሻ ሳር ቤት
ከካናዳ ኤንባሲ ፊት ለፊት

Galleria TO.MO.CA
Location; Sar Bet
In front of Canadian Embassy
www.galleriatomoca.com